ጠርጥሬያችሁ አይደለም ያስማልኳችሁ። ነገር ግን ጂብሪል መጥቶ አላህ በናንተ መላእክትን እንደሚፎካከር ስለነገረኝ ነው።› አሉ።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ሙዓዊያ በመስጂድ ውስጥ ክብ በሰሩ ሰዎች ላይ መጣና "ምንድን ነው
ያስቀመጣችሁ?" አላቸው። እነርሱም "የተቀመጥነው አላህን ልናወሳ ነው።" አሉ። እርሱም "በአላህ ስም ማሉልኝ ከዚህ በቀር ሌላ አላስቀመጣችሁምን?" አላቸው። እነርሱም "በአላህ እንምላለን ከርሱ በቀር ሌላ አላስቀመጠንም።" አሉ። እርሱም "ያስማልኳችሁ ጠርጥሬያችሁ ሳይሆን በኔ ደረጃ ላይ ያለ ሆኖ ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከኔ ያነሰ የሐዲስ ብዛት የዘገበ የለም። የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ክብ በሰሩ ባልደረቦቻቸው ላይ መጡና
‹ምንድን ነው ያስቀመጣችሁ?› አሉ። እነርሱም ‹የተቀመጥነው አላህን ልናወሳውና ለኢስላም ስለመራንና ኢስላምን ለኛ ስለለገሰን ልናመሰግነው ነው።› አሉ። እርሳቸውም ‹በአላህ ስም ማሉልኝ ከዚህ በቀር ሌላ አላስቀመጣችሁምን?› አሏቸው። እነርሱም ‹በአላህ እንምላለን ከርሱ በቀር ሌላ አላስቀመጠንም።› አሉ። እርሳቸውም ‹ጠርጥሬያችሁ አይደለም ያስማልኳችሁ። ነገር ግን ጂብሪል መጥቶ
አላህ በናንተ መላእክትን እንደሚፎካከር ስለነገረኝ ነው።› አሉ።"» [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ሙዓዊያ ቢን አቡ ሱፍያን (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና መስጂድ ውስጥ ክብ ወደሰሩ ሰዎች መጡና ለምን ጉዳይ እንደተሰበሰቡ ጠየቃቸው። እነርሱም "አላህን እያወሳን ነው።" አሉ። ሙዓዊያም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና በመቀመጣቸውና በመሰብሰባቸው አላህን ከማውሳት በቀር ሌላን እንዳልፈለጉ አስማሏቸው። እነርሱም ማሉላቸው። ቀጥሎ "በእውነተኝነታችሁ ላይ ጠርጥሬያችሁ አይደለም ያስማልኳችሁ።" አሏቸው። ቀጥሎም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ እንደርሱ ቅርብ የነበረና የርሱ ቅርበት እህቱ ኡሙ ሐቢባም የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሚስት ስለነበረችና እርሱም ወሕይ ፀጸሐፊ ስለነበረ ነው። ከመሆኑም ጋር ግን ጥቂት ሐዲስ ያስተላለፈው እርሱ እንደነበር ተናገረ። አንድ ቀን ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከቤታቸው እንደወጡና መስጂድ ውስጥ ተቀምጠው አላህን እያወሱ፤ አላህ ለእስልምና ስለመራቸውና እስልምናን ስለለገሳቸውም እያመሰግኑት አግኝተዋቸው ልክ ሙዓዊያ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ባልደረቦቹን እንዳስማላቸው ሁሉ ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጠይቀው እንዳስማሏቸው ተናገረ። ቀጥሎም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እነርሱን የጠየቁበትንና ያስማሉበትን ምክንያት ተናገሩ። እርሱም መልዐኩ ጂብሪል የአላህ ሰላም በርሱ ላይ ይስፈንና እርሳቸው ጋር መጥቶ አላህ በናንተ መላእክቱን እንደሚፎካከር የናንተንም ደረጃ ለነርሱ እንደሚገልፅ፣ የስራችሁን ውበት እንደሚያሳያቸውና እነርሱ ዘንድም በናንተ ላይ እንደሚያወድስ ነገረኝ አሉ።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/3007